የመንጐሌ ጥሪ «ብዕር ንቀል!»

ይላል።



# ኃይሉ (ገሞራው)

ፍንዳታ – ቁጥር 101

ስቶክሆልም — 1994

# አ ዝ ማ ች

ፀርግዋ ካላዋጣ — በመንፈስ መታገል ፤

ነፍስን በመለወጥ — ጠባይ ማስተካከል ፤

ሌላ አማራጭ የለም — በስተቀር በአካል ፤

ሥጋን ጨፈላልቆ — ካልፈጠሩ አምባል፤

ስለዚህ የወረቀት — ትግሉ ይበቃል ፤

የመንነሴም ጥሪ — "ብዕር ንቀል!" ይላል፤

———XXXXXX———



# ለ ዘ መ ኑ ት ግ ል

በመንፈስ (የነፍስ)



ይህኛው?

የሚያበጣብጠን — ቢሆን ድንቁርና ፤

የመንፈስ ትግል ነው — አጣቢው ግሙና !

## ወይስ?

# ለ ዘመኑ ትግል

የርስዎ ግላዊ ምርጫ የትኛው ነው ?




ፀጥባዉ ከሆነ — ድንቁርናም ዕውቀት ፥

የሥጋም የነፍስም — ትግል ነው መድኃኒት !



" አቅረብኩ ለከ እሳተ ወማየ ደይ እዴከ ኀበ ዘትፈቅድ ! "

እንዳለው ሳንቲካዊው መጽሐፍ

የዓለማችን መዋቅራዊ ባሕርይ ሆኖ፥ ያሉን አማራጮች እንደ እሳት ጡት መንታ ወይ ናቸው። የከረረ ወይም የረገበ ። በትግልም እ እንዲሁ መንታ አማራጮች አሉ ። ዘመንፈስ (የነፍስ) ወይም ዘሥጋ (የአካል) ። የመንበ ትግል ፊታውራሪው አዝማችም ሆነ ደጀኑ መካች ብዕር ነው ። የአካሉ ደግሞ ባሩድ ነው ። እንደሰው ፍጡርነት ደገኛው አማራጭ የመንፈስ ትግል ነው ። ያ ባይሆን ኖሮ፥ እንደ አውሬዎቹ ፍጡራን፥ መዋጊያ ቀንድ ወይም መጊጠሚ ጥፍር መርገጫ ሰኮና ማባረሪያ ጭራ . . . ወዘተ በኖረን ነበር።

ስለዚህም፥ በበኩሉ የምንጊዜውም አማራጭ የመጀመሪያው ዓይነት የመንፈስ ትግል ነው። በሰላ ብዕር ጠላትን ነድፎ መጣል እንደሚቻል ተሰ ቶዶም እምነቴም ነው ። ይሁን እንጅ ይህ የትግል ዘርፋዊ አማራጭ እማያዋጣና የማያመረቃ ከሆነና ብዙኃኑም ካላመኑበት ሌላውን መሞከር ግድ ይላል ። ይህች ግጥም ሁለቱንም የትግል አማራጭ ዘርፎች በማ መላከት፥ በመሠረታውያን ንድፈ ሐሳቦች ላይ ትሽከረከራለች። ውሳኔ መስጠቱ ግን የአንባብያን ብቻ እንደሆነ ትጠቁማለች ።



# የመንጐሴ ጥሪ

# «ብዕር ንቀል!» ይላል።





እንደርዳሪው አዝማች !

በርግጥ ካላዋጣ — በመንፈስ መታገል ፤
ነፍስን በመለወጥ — ጠባይ ማስተካከል ፤
ሌላ አማራጭ የለም — በስተቀር በአካል ፤
ሥጋን ጨፍላልቆ — ካልፈጠሩ አምሳል ፤
ስለዚህ የወረቀት — ትግሉ ይበቃል ፤
የመንጎሌም ጥሪ — "ብዕር ንቀል!" ይላል ።

---------XXXXXX---------

## የመንጐሴ ጥሪ
## «ብዕር ንቀል!» ይላል።

‹ ይሁኝ ውሉዱ — ወውሉደ ውሉዱ ፤
ወእጓልደ — ውሉዱ › ፤
ብለው ግለቢያውን — ሲያደርጉት ‹ ይደምሰስ › ፤
ያን ዘመን ነበረ — ሞት ብለው ሰዎች ፈጣሪ ክርስቶስ ፤
በሰተ-ሥቅለቱ — ያ ሁሉ እልቃሽ ሲያለቅስ ፤
ወጃፈያ መንጎሌ — ብዕር የተከለው ፤
ያልታሹን ደም ዕንባ — ቀለም ያደረገው ፤
ገድሉን ሥንክሣሩን — ሊጽገብ ያቀደው ፤
ብሶትን መከራን — ከነዝባዝንኬው ፤
ይደምሰስ ለማለት — ሐቅ ይዞ የቆመው !

ከዚያ ሁሉ መግር – ከዚያ ሁሉ ቀለም ፥
መብላቷን ተረዳሁ – ብናኝ ሆኑ ዘደም ፥
ናትና ሐቀኛ – በዛሬው ወቅ ንለም ።

መንፈስ በመግረክ – ካላስገበረ ንካል ፥
ምንም ቱይላ አልሠሩም – የወረቀት ትግል ፥
ስለዚህ ቀይር – ዘዴውን ሊያገኝል ፥
አለመትርው ጠባይ – ፊልሳ "ወድር!" ሊል
የመንገሱ ዋሬ – "ብዕር ንቀል!" ይላል ።

------XXXXXX------

ለትዝታ ያሀል – ትላንትን ብታዘብ ፥
የዛሬ ጅል ናፎል – ከልል የቆመ ዘብ ፥
ብርሃን እንዳይመጣ – ኬላ ልዩ ገዳብ ፥
በጭለማ ሊያኖር – ፀሐይን የሚሰድብ ።
የትላንቷ ዝምብር – ከዳመና ከኑም ፥
ስትታገል ነበር – ጭለማን ለማወደም ፥
ጭጋግን ብታመልጥ – ውርዉን አልቻለችም ፥



እንደዚያም ሆኖና – ዛሬ አልታየችም ።
እኔም እንደዝምብር – ከዛሬ ደርሼ ፥
ማምረት እወኝ ነበር – እንዳቅሜ አርሼ ፥
ትላንት ዓለኝ እንጅ – መንገል ተንተርሼ ።
ስጭር ናሬ ነበር – በወረቀት ማሳ ፥
ዘርቼ ለማምረት – የውቀት ፋልማሳ ።
ስፍቅ ናሬ ነበር – የወረቀት ደረት ፥
አብለዉልዌ መስሎኝ – የውቀት መስታዎት ።
አርሻ ውዬ ነበር – ለማምረት ገቢና ፥
አረም ጭጠው እንጅ – ኮትኳች ሰው አጣና ።
ባንድነት ጠምጄ – መንገል ከብዕር ጋር ፥
ዕውቀትን ለመገረት – ተመኝቼ ነበር ።
ሠራዊት ብዕር – እንደኔ ከሆነ ፥
ይዘቀዛል መግር – መስኗል የመከነ ፥
ጀሉቱዊ ምርትህ – ዘርማጥ የሚወን፥
ውጤት አልባ ትግል – ሆኗል የባከነ ።
ደራሲ ገበሬ – ቀንበርህን ፍታ ፥
ብዕር አዋጥዋም – ለመሆን ወከታ ፥
ዕውቀት አምርቶ – ከቱትን ሊገታ ፥
ድንቁርናን ገጭቶ – አልቻለም ሊመታ ።



## እኔን ያዝለፍልፈኝ !

[illegible]

---------XXXXXX---------



# «ብዕር ንቀል!» ይላል።

ትትርቱ መገሉ – ብዕርህ ግረኛው ፥
ምርቱ ካላረከ – መጣጣሩ ይብቃው ፥
ቀንበሩን ፈታተህ – መደዱር ልቀቀው ፥
የዚያ ብናኝ ትግብርት – ነውና መፍትሔው ፥
በወረቀት ግባ – ግምረት ለተሳነው ።

የኔግ መንኳሌ – ባባለሌው ጥሬ ፥
ብዕር ንቀል ይላል – አልሠራም ቲአሬ ፥
ተግባር ነው ይለኛል – ሥርዓት አስከባሪ ።

መንፈስ በመግረክ – ካላስገበረ ኀካል ፥
ምንም ቱይዳ አልሠራም – የወረቀት ትግል ፥
ስለዚህ ቀይሮ – ዘዴውን ሊያቫሽል ፥
አለመትርው ጠባይ – ፈልጎ "ወድር!" ሊል
የመንኳሌ ጥሬ – "ብዕር ንቀል!" ይላል ።

------XXXXXX------

ይመስለኝ ነበረ – በሳይገሉ እንነገር ፥
ቲአሬ በተግባር – ቀድሞ የሚጀምር ።

አድርገው ይለኛል — መነኩሴ እንዳይመክን ፤
ወረቀቱን ሲጥር — ውስጥ ውስጡን እንዲያፍን ።
አስተካክሎ እንዲጥር — አቀናጅቶ በሕግ ፤
ሠራዊት ሹራን — በሥርዓት እንዲጠርግ ።
ለነፍስ ብቻ መከተብ — ምንም አላጥቅም ፤
ለመንፈስ መግባር — ባለቤን አልቀባም ፤
ለኅሊና መጸፍ — ውጤት አላመጣም ፤
ሥጋን እንጂ እንግዲህ — ከገባበት ገብቶ ፤
አባርሮ መግረፉ — ደፋር ልቡ አግኝቶ ።
ለሥጋ እንጂ እንግዲህ — ጥጋ ፅሑፉን መስጠት ፤
እንዲያገኝ መግባር — ተገቢውን ቅጣት ።
ለሌውግ መግር — ምንም ትርጉም አጥቷል ፤
ቀለም ከወረቀት ጋር — ሲያባክን ሰንብቷል ።
የወረቀት ነብር — እየሆነ ድመት ፤
ካይጦች በስተቀር — አልጊጠጠም ከፋት ።
የወረቀት ነብር — እየሆነ ፍየል ፤
ከቅጠል በስተቀር — አልበጠሰም አወል ።
የብራና አንበሳ — እየሆነ አህያ ፤
ከሠርዶ በስተቀር — አልነቀለም ቃሪያ ።
የወረቀት አነር — እየሆነ አይጥ ፤
አልቻለም ለማረም — የተንኮልን ማገጥ ።
ታዲያ ምን ይጠቅማል — ፲ ጊዜ ወረቀት ቢያክ ፤
ጠራርጎ ካልጣለ — ፎብያ ማንያክ ፤
ያ ብዕር አጅሬ — ቢያሳምር አስካክ ፤
ከመንኅሉ ግፍ ላይ — ተገትሮ ቢውብክ ፤
ግራ ነኝ እያለ — ቢያቅራራ ቢጓክክ ።
ስለዚህ ይለኛል — የሰለቸው መንኅል ፤
እንዲያ ካለው ብዕር — ነቅለህ ተገላገል ፤
ጥይት የሆነ እካል — በምትኩም ትከል ።

በርግጥ ካላጥቃ — በመንፈስ መታገል ፤
ነፍስን በመለወጥ — ጠባይ ማስተካከል ፤
ሌላ አማራጭ የለም — በስተቀር በአካል ፤
ሥጋን ዉፈላልቶ — ካልፈጠሩ አምሳል፤
ስለዚህ የወረቀት — ትግሉ ይበቃል ፤
የመንኅሉም ጥሪ — "ብዕር ንቀል!" ይላል
------XXXXXX------

ይለኛል ካንጀቱ — የብዕር መንኅሉ ፤

ስታውቅ ምኝ አትሁን — እያታለህ ሙሌ ፤
ወረቀት ላይ መጣር — በብዕርህ ሁሉ ፤
ብቻውን አይበቃም — ለነገለመሌ ።

እንዲያ ጥር ጥር — ሕይወቱን በሙሉ ፤
ውጤት ካላሳየ — ከብዙው ከሌሉ ፤
ከቶ ምን ይጠቅማል — ብዕሩ መንሳቱ ።

በሚሰጠው ትምህርት — ካልሰጠ በረከት ፤
ምንድነው ትርጉሙ — መጣር በወረቀት ።

ካላስተካከለ — ጉዴሉን ከዶርቢ ፤
ሲላግን ከጋላ — ወመቴን ከመንጌ ፤
ከቶ ምን ይጠቅማል — መጣሩ ሁልጊዜ ።

ካላስከበረ እኩል — እንጨን ከትግሬ ፤
ጉራጌን ከአፋር — ቀቱን ከጎንደሬ ፤
ወላሞን ከብሌን — ጎጃሜን ካደሬ ፤
ከቶ ምን ፋይዳ አለው — መጣሩ ብዕሬ ፤
ብዕር በሬ አይደል — አያወርትም ፍሬ ።

ወይም በሬ አይደለም — ማጥር አያወርት ፤
ወይም ሠንጋ ሆኖ — ሥጋው አያስደስትም።

በሚጥረው ቃሉ — ውሕደት ካልፈጠረ ፤
ወንደሩን ከእምባ — ካላስተባበረ ፤



ንፃምና ደብሩን — በአንድ ካላኖረ ፤
ሰፈር አገናኝቶ — ሰው ካላፈቀረ ፤
ብዕር ብቻ ቢጥር — ምኑ ምን አገረ !!

ብዕር ስለት ካጣ — ዶልዱም ቢደንዝ ፤
ለሰላሳውን መንፈስ — ቢሳነው መገዝገዝ ፤
ምን እግራቂ አለው — በስተቀር ከግዝዝ ፤
ለዚያ ለመንጉሴ — ለኖረው ሲተክዝ ፤

መንፈስ በመግረክ — ካላስገበረ ነካል ፤
ምንም ፋይዳ አልሠራም — የወረቀት ትግል፤
ስለዚህ ቀይሮ — ጸዴውን ሊያቀኝል ፤
አለመትርው ጠባይ — ፈልጎ "ወድር!" ሊል
የመንጉሴ ጥሪ — "ብዕር ንቀል!" ይላል ።

-------XXXXXX-------

‹ነቅለህ ጣል !› ከማለት — ሌላ ምን ሊኖረው ።
መኖረድ አይቻልም — በመንጉሴ ነገር ፤
እግራቂ የሌለው — ነውና ባይተዋር ፤

# የመንግሉሴ ጥሪ

የወረቀት ፍቅር — በርግጥ ካላጣ ፤
መከላት ይቻል የለ — እንላሿሬ ጠጣ ።

የመንነሉስ ብዕር — ደንዞ ካሸረ ፤
መተካት ይቻላል — ጨሶ ካልከሸሬ ፤
በሆነ ራስናበር — ድንበር ካላለሬ ።

በርግጥ ካላጣ — በመንፈስ መታገል ፤
ነፍስን በመለወጥ — ጠባይ ማስተካከል ፤
ሌላ አማራጭ የለም — በስተቀር በአካል ፤
ሥጋን ጨሬላልቶ — ካልፈጠሩ አምሳል ፤
ስለዚህ የወረቀት — ትግሉ ይበቃል ፤
የመንነሌም ጥሬ — "ብዕር ንቃ!" ይላል

---------XXXXXX-----------

በመንፈስ ይባላል — የወረቀት ትግል ፤
አነጣጥሮ ተኳሽ — ለጎሊና ነኀል ፤
ለዚያ ለአፅምሮ — ለረቂቁ ኃካል ።

ቲአሬ ይባላል — ሥርዓተ ቅላሴው ፤
የአራራይ የዕዝል — ግዕዛዊ ዜማው ፤
ለልብ ለጎሊና — ለመንፈስ ቀራቢው ።




ለ ወ ድ ሬ ን  ነ በ ረ !

[illegible]

---------XXXXXX---------

ለገዋ ደንቆሮ — ለባዶ ባዳንዋ ፤
ምኑን ያስተምሩታል — መንፈሱ ለነዋ !
ከንቱ መታከት ነው — በከንቱም መድከም ፤
አውቆ የደነቆረን — በብዕር ማከም ።
በወረቀት መምታት — ደንቆሮን ከፀር ፤
ከንቱ መጫጫህ ነው — መደናፀር አብሮ ።
በሚገባው ቋንቋ — በሚገባው ብሒል ፤
ማስተማር ግድ ይላል — የደንቆሮን ቀላል ፤
ያንጊዜ ያውቀዋል — ምንነት ሰው ሲባል ።
ያለዛ ከንቱ ነው — ማስተማር መተረክ ፤

በርግጥ ካላዋዋ — በመንፈስ መታገል ፤
ነፍስን በመለወጥ — ጠባይ ማስተካከል ፤
ሌላ አማራጭ የለም — በስተቀር በአካል ፤
ሥጋን ጨፈላልቆ — ካልፈጠሩ አምሳል ፤
ስለዚህ የወረቀት — ትግሉ ይበቃል ፤
የመንፈሱም ጥሪ — "ብዕር ንቀል!" ይላል

———————XXXXXX———————



ሞራል ፍልስፍና — ክብረ ሰብን መምበክ ፤
እንዲያ ዓይነቱን ሰው — በብዕር መግረክ ፤
በወረቀት ጎራ — በብዕርም መድረክ ።
የምን አርስቶትል — የምን ሲድራቅ ሚባቅ ፤
የምን ሔሮዶቱስ — የምን ማርክስ ይስሐቅ ፤
የምን ቴዎድሮስ — ምኒልክ ያሬድ ሊቅ ፤
ዘላለም ላይገባው — በከንቱ መላረቅ ።
በሚገባው ቋንቋ — በደረቁ ብሒል ፤
ነው እንጂ ማስተማር — የደደብን አካል ፤
እንደገል ቀጥቅጦ — እንዲሆነው አንኳል ፤
እንደሰም አቅልጦም — እንዲወጣው ፀወል ፤
ያ ነው አማራጩ — ለንደዚያ ዓይነት ቀላል ።
የየትም ሀገር ሕዝብ — ነባር ታሪክ አለው ፤
ሰላለፈው ትውልድ — ግወቅ የሚረዳው ፤
መስተዋቱ ሆኖት — የሚያይበት መጪው ።
ትላንትና ሞቷል — ብለን ባለመናቅ ፤
ለሕያዉ ዛሬ — ቅርስ እንዳለው ማወቅ ፤
ለትንቢቱ ነገም — እንደናስቀምጥ ሥንቅ ፤
ታሪክ ይረዳናል — ለዚህ ነው መስተዋት ፤
በሐቅ እስካየነው — ነውና አብነት ፤

መግፊያ መታጠቅ – አለመታጠቅ ነው ።

ያ እንዳይሆን ነበር – ወረቀት ከብዕር ፤

ተጋብቶ መኖሩ – ባንድነት ሲግባር ።

ያ ዘዴ እንዳልሠራ – ከታወቀ ዛሬ ፤

ወንጌሌ ይለኛል – "ይነቀል ብዕሬ!" ፤

"ቀይር" እንደማለት – ብስልን በጥሬ ።

ወንጌል ለመግረክ – ካላስገበረ ኃካል ፤

ምንም ፋይዳ አልሠራም – የወረቀት ትግል ፤

ስለዚህ ቀይር – ዘዴውን ሊያሻሽል ፤

አለወትሮው ጠባይ – ፈልጎ "ወድር!" ሊል

የወንጌሌ ጥሪ – "ብዕር ንቀል!" ይላል ።

------XXXXXX------

ሐዋስ ተሰቶ እሚያደርስ – አዲስ ዘዴ ልዩ ፤

ጠብመንጃ ነው አሉኝ – ምፅራፍ ድልድዩ ።

የፅፅሞት ሳይሆን – ፅጥናዊ ጭሱ ፤

ድኝ ነው ይሉኛል – ባሩዳዊ ልብሱ ፤

ግፅጠንተ ሕይወት – ነፃነት ሲያድሱ ።



ጥበበ ድኝ ነው – አባት ያዲስ ሕይወት ፤

መዳኛው መድኃኒት – ላቂ ከወረቀት ፤

ፈዋሹ በቅጽበት – ነፃ አውጭ አብነት ፤

ለጊዜው ቢመርም – ባይጥምም እንደሬት ።

ሲጠለዝ ነውኮ – ታምቡሩ ከበሮው ፤

ሲነሰም ነጋሪት – ሲነረት አታሞው ፤



ሲወታ ሲወገር – ሲጠፈጠፍ ዲቢው ፤

ከውስጡ ካካሉ – ተሠምሮ ያለው ፤

ጣዕሙ ቅላጼው – ነርሮ የሚወጣው !

ሲጠለዝ ነውኮ – ታምቡሩ ከበሮው ፤

ሲነሰም ነጋሪት – ሲነረት አታሞው ፤

ሲወታ ሲወገር – ሲጠፈጠፍ ዲቢው ፤

ከተባለ እንግዲህ — ሞራል ደኅና ሰንብት !
በምን ሊዳኝ ይሆን — ትምክሕትና ዕብሪት!
ሊያስፈልግስ ይሆን — ማስተማር ትምህርት?
ጉልበትና ቀመኛ — ከተካው ያለፍረት ÷
ኅሊና ካልሆነ — መለኪያችን መሥፈርት ።
ዕውቀት ካልሆነ — የሰው ፊታውራሪ ÷
ደደብና ማይምን — ከተባለ ወሬ ÷
በጉልበቱ ብቻ — ከሆነ ተፈሪ ÷
ግሑሱ ግዕምር — ቁም ነገሮች ሠሪ ÷
ምን ሊደረግ ይሆን — ይጠየቅ ፈጣሪ !
የሕዝቦች ፍላጎት — ካልሆነ መሥፈሪያ ÷
ኢዲሞክራሲ ነው — የጉልበት መግሪያ ።
ጉልበት ከወሰነው — የሕዝብን ፍላጎት ÷
ትርጉም አይኖረውም — የሰዎች ነፃነት ÷
ፍትሕና ርትዕ ሆነ — በጠቅላላውም መብት ÷
የያንዳንዱ ኑሮ — የምንለው ሕይወት ።
ዝለዚህ ኪደቶች — ልዩ ዕድገት ቢያሳዩ ÷
ለጊዜው ነው እንጂ — ወገን ቢለያዩ ÷
ዘላቂ አይደሉም — ወራትም አይቆዩ ።
የጉልበት ውግኔ — የሸምጤቆ በትር ÷



ንጥር ሐቅ ሲያገኘው — ወዲያው የሚሰበር ÷
ስለሆነኮ ነው — የመንጎሌን ምክር ÷
እስካሁን የቆየሁ — ባሰላ ስቀምር ÷
ያዋጣ አያዋጣ — እንደሆን ሳዘክር ÷
ጥሪ ሳልቀበል — የዘገየሁ ለወር !!
የጥሪውን ክልል — ዙሪያ ገረገቡን ÷
በምርምር አግሬ — ዞሬ ያየሁትን ÷
እንድባንድ ዘርዝሬ — ባላወራም ሁሉን ÷
አመላክቻለሁ — ዋናውን ጉሉሁን ÷
በኅሊና ባካል — መካከል ያለውን ።
እንግዲህ እናንተ — ወገኖች ፍረዱ ÷
ጥሪውን ልቀበል — ልጓዝ በመንገዱ !
ወይስ በብዕሬ — ይቀጥል ምገዱ ÷
በቃላት በሐረግ — ምግታር መገድገዱ ።
ኅሊና ሳይጠራ — አዕምሮ ሳይዳብር ÷
ንካላዊ ትግል — ዕውነት ሳያነጥር ÷
ከንቱ ነው ይላሉ — የየመሰኩ ምሁር !
የትግሉ ሁሉ — የተግባር ቀዳሚው ÷
ሥነ ቃል ቲአሪ — የመንፈስ እንጂ ነው ÷
እንደዮሐንስ መጥምቅ — ጎዳና ጠራጊው !

ብዕር ከወረቀት - እናከሠው የጣሩት ፤
ስለነበረ ነው - የተሻለ መንገድ ፤
ከቡሩን ብፀፅ ሰው - በባሩድ ከማንደድ ፤
ጎሊናውን ማርከው - ከፉት ለማስወገድ !
ጠዋት ማታ የጣሩት - መታከስ እንዳይለምድ ፤
እንዳይማገድም - ከጦርነት ምገድ ።
ከ "ነቀለ" ኋላ - "ወድር" ን ሊያስከትል ፤
የመንጎሉ "ጥሪ" - ብዕር ንቀል ይላል ።



ከእንግዲህ ይብቃህ - መንቀሳቀስ ብዕር ፤
ጉልበት ተተክቷል - መንፈስ ለማስገበር ፤
ያንተ ዐቅም አልቻለም - አመፅ ለማባረር ።



ብዕርማ ነበር - የአመፅ መድኃኒት ፤
ጠራርጎ የሚያጠፋ - የኀሊናን መቅሠፍት ።
ተቀባይ ግን ካጣ - ሰሚ ያለው ጆሮ ፤
ቦታውን ይለቃል - ለጣሳ ቀርቀሮ ፤
በጥይት በባሩድ - ለሚያወልክ ደንቆሮ ።
ግን እሁንም ቢሆን - ተስፋ ባለመቁረጥ ፤
ብዕረኛን ሁሉ - ልጠይቅ ቢያሳምጥ ።
እንዳጸጂነታችሁ - ልብና ኅሊና ፤
እላችሁ ወይ እንደድ - የመንፈስ ባሙና ፤
ቀኜ ዕቡያንን - የሚያጥብ ፀጸምና ።
ፀርግጥ ማጠብ ችሎ - እድፍ የሚያስወድ ፤
የቆሸሸ ልብን - የሚያጸዳ በግድ ፤
እላችሁ ወይ ጥበብ - የፋውንዴሬ ሞድ ።
ያንን መሳይ ጥበብ - ካለ ባደባባይ ፤
ሰውን ከመግደሉ - እኛ የለን ጉዳይ !
ብዕረኛ ሁሉ - ሲደግ የኖረው ፤
ፀብዕር እፍንጫው - ሁሌም የተዋጋው ፤
ለማስቀረት ነበር - ሰውን ከሞት ፅጣው ።
ሁሉ ሰው እምናፀት - ሌላ ፀዴ ካጣ ፤
ከእንግዲህ እመሩኝ - ነብተናል ከጣጣ ፤

# ትግልክ ኪደት ነው!

(ሙዚቀኛው ዘነበ በናታ እንደጻፈው)

March Tempo :







Giutar One :    March Tempo :



Guitar Two :    March Tempo :



# Struggle is a process!

Tener Saxphone One : March Tempo :



Tenor Saxophone Two :





# ትግልኮ ኪደት ነው!

Bass Guitar One : March Tempo



Bass Guitar Two :



## Struggle is a process!

First Violin One :                March Tempo :



First Violin Two :





## ትግልክ ሂደት ነው!

Second Violin One :                March Tempo :



Second Violin Two :



# Struggle is a process!

Trumpet In G One :

March Tempo :



Trumpet In N Two :





-----------xxxx-----------